የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዝያ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ቁጥር	ርእስ/ንኡስ ርእስ	ገፅ
ክፍል አንድ	መግቢያ	3
1.1.	የጥቱ ዳራ (Backgraound of The Study)	3
1.2.	የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ	4
1.3.	የጥናቱ ዓላማ	5
1.4.	የጥናቱ ወሰን	5
1.5.	የጥናቱ አስፈላጊነት	6
1.6.	መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች	6
ክፍል ሁለት	ተዘማጅ ፅሁፎች ትንተና	7
ክፍል ሶስት	የጥናቱ መረጃ አሰባስብ ሂደትና ትንተና ዘዴ	9
3.1.	የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research Design)	9
3.2.	የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)	9
3.3.	መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data Collection Methods)	9
3.4.	የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ	11
ክፍል አራት	የሙስና ስጋት መረጃዎች ትንተና	12
4.1.	የተቋማት አደረጃጀት	12
4.2.	ተጠያቂነትን ማስፈን	14
4.3.	የተቋማት ግልጽነት	17
4.4.	አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ	18
4.5.	የተቋማት ንብረት አስተዳደር	20
4.6.	የግዥ አስተዳደር	21
4.7.	የሰው ሃብት አስተዳደር	24
4.8.	የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ	25
4.9.	የፕሮጀክቶች አስተዳደር	26
4.10.	ኦዲትና ቁጥጥር	27
4.11.	የሙስና ስጋት	29
ክፍል አምስት	መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	31

5.1.	መደምደሚያ	31
5.2.	የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	32

ክፍል አንድ
መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ እድገት እና የሰብአዊ መብት መከበር በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዳ፤ ባለስልጣኖች ከህብረተሰቡ የተሰጣቸውን አደራ ለግል ጥቅም በማዋል የሀገርን እድገት የሚያቀጭጭ፤ ሐቀኝነትን የማጉደል ወይም ሕገወጥ ባህሪ ማለት ነው፡፡ ይህም ሙስና የህግ የበላይነትን በማጣመም እና ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን ተቋማዊ መሰረት በማቀጨጭ ልማትን ያዳክማል፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማነቆ ይሆናል፣ በመሰረተ ልማት፣ በተቋማት እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማዳከም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ያጎለብታል፣ የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆልን ያመጣል፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እንዲሁም ሀብታቸውን አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ የተለያዩ ጥናቶች በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን ለሙስና ስጋት የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣

አደረጃጀቶችና አሰራሮችን በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሰራቱ፣ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን አደራጅቶ ወደ ተግባር ቢገባም እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

በተለያዩ ዘርፎች ስር በሚገኙ ተቋማት ሊከሰቱ ለሚችሉት የሙስና ዓይነቶች፣ የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ሥርዓት፣ የግለሰቦች የሥነ-ምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራርብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት … ወዘተ እንደ ተቋማዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መቃኘት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

ይህ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ሪፖርት በኢኖቬሽን ቴክኖሎጅ ዘርፍ ከሚገኙ አምስት ተቋማት የተሰበሰቡ መረጃዎች መሰረት በማድረግ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከያ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

1.2 የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍን የሚመራው ተቋም ለመጀመሪያ ጊዜ በኮሚሽን ደረጃ በአዋጅ ቁጥር 62/1968 ዓ.ም እንደተቋቋመ፤ በመቀጠል በ1997 ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ በሚል እንደገና ተደራጅቶ በድጋሚ የኢፌዲሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በማለት በአዋጅ ቁጥር 603/2001 እንዲሁም በ2011ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በመባል በስሩ 4 ተጠሪ ተቋማትን (የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ጂኦ-ስፓሻል ኢንስቲትዩት፣ የባዮና ኢመርጅንግ ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት እና

የኢትዮጵያ ቴክኖሎጅ ባለስልጣን) በአጠቃላይ 1087 ሰራተኞች በመያዝ እየሰራ እንደሚገኝ ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የዘርፉ ዋና ዋና አላማዎችም፡-

- ፍላጎትን መሰረት ያደረገ እና የቀጣይ ዘመን ኢንዱስትሪ ውስጥ በብቃት የሚሳተፍ የሰው ኃይል የሚፈጠርበትን ሥርዓት መዘርጋት፣
- ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር፣ እንዲሁም ለኢኖቬሽን መደላድል ለመፍጠር የሚያስችል መሰረተ-ልማቶችን በቀጣይነት ማልማት፣
- ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ቢዝነስን መሠረት ያደረጉ ኢኖቬሽኖችን በማበረታታት ለስራ ዕድል፣ ለሃብት ፈጠራና ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (GDP) ዕድገት የሚኖረውን ድርሻ ማሳደግ፣
- በቴክኖሎጂ ልማትና ኢኖቬሽን የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ መሪነቱን ማረጋገጥ፤
- የሀገር በቀል ዕውቀቶችን በማልማት ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል የአደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓትን በመፍጠር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ባህል መገንባት፣
- የተቋማት ትስስርና ትብብርን በማጠናከር ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ አጋርነት እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣
- የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር ሀገራዊ የፈጠራንና የኢኖቬሽን እንቅስቃሴን መደገፍ፤
- የቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ስራዎች የማህበረሰቡ እሴትና ሞራል የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- በስፔስ ሳይንስና ጂኦስፔሻል ዘርፍ ምርትና አገልግሎቶችን ለመጠቀም፣ ለማላማድ፣ ለማሻሻልና ለማምረት የሚያበቃ የስልጠና አገልግሎት መስጠት እንዲሁም መረጃዎችን ለማሰባሰብ በማምረትና ተደራሽ በማድረግ ሀገራዊ የልማት ስራዎችን መደገፍ፣

1.3 የጥናቱዓላማ (Objective of the Study)

አጠቃላይ ዓላማ፡-

የዚህ ግምገማዊ ጥናት ዋና ዓላማ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ ዘርፍ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

ንዑስ አላማዎች፡-

- የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

የጥናቱ ወሰን

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ከህዳር/06/2015ዓም እስከ ሚያዚያ/30/2015ዓም ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በመባል በስሩ 4 ተጠሪ ተቋማት (የኢትዮጵያ አፅምሯዊ ንብረት ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ጂኦ-ስፓሻል ኢንስቲትዩት፣ የባዮና ኢመርጅንግ ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ቴክኖሎጅ ባለስልጣን ላይ ተቋማዊ ተጠያቂነት፣ ግልፅነት፣ አዋጅ ደንብና መመሪያ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር የግዥ አስተዳደር፣የሰው ሃበት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና ኦዲትና ቁጥጥር የአሰራር መርሆችን መሰረት በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡

የጥናቱ አስፈላጊነት

የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በአሰራር እና የስራ ሂደቶች ውስጥ የሚታዩ ድክመቶችና ብልሽቶች በመለየት የሙስና ቅደመ መከላከል እድል ስራዎች ለመተግበር የሚግዝ መሳሪያ

ነው፡፡ ዋናው የግምገማዊ ጥናቱ አላማም የሙስና ስጋቶች በተጨባጭ መረጃ በተደገፈ በመለየት የመከላከል ስልቶችን እና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ማስቻል ነው፡፡ እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ የአደጋ ለውጦችን ለመከታተል ለፀረ-ሙስና ትግል ሥራ እንደ መነሻ ሆኖም ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዚህ መሻነት ይህ ጥናት በማዕድን ዘርፍ የሚታዩ የሙሰና ስጋቶች በአስራ አንድ የትኩረት ጉዳዮች ለመየት የተካሔደ ነው፡፡ ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ፋይዳው በማዕድን ዘርፍ የሚሰሩ መንግስታዊ ተቋማ የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የስራ ዘርፎችንና የአሰራርር ስርዓቶችን በመለየት፣ የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ በማመንጨት የሙስና መከላከል ስልት ማመላከት እና በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

ጥናቱ ሲካሄድ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ችግሮች አጋጥመዋል፡፡

- የተቋማት ኃላፊዎች/ሰራተኞች በተያዘላቸው ቀጠሮ ያለመገኘትና ጥናቱን የሚያከናውኑትን ባለሞያዎች የማመላለስ፣
- የተቋማት ኃላፊዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣
- በተቋማት የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ችግር መኖር፣
- የሥልክ፣ የትራንስፖርት፣ የሰው ሀይል እና የጊዜ እጥረት፣

ክፍል ሁለት

የዘርፉ ሙስና ስጋት ጥናት ተዛማጅ ፅሁፎች ዳሰሳ

ሙስና ባላደጉ አገሮች ብቻ ሳይሆን ባአደጉት ሃገራት ጭምር የሚታይ ጎዳይ ነው። በተለያ ጉዳዮች ላይ ከሙስና ጋር የተያያዙ ጥናቶች ቢካሄዱም በኢኖቬሽን እና ጤያዝ ጎደዮች ጥልቅ ጥናቶች ማግኘት አስቸጋሪ ነው። በዘርፉ የሚታውን ሙስና ጥናት የማካሔድ ልምዱም ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል (Julia Golla, 2010)። ድርጅቶች ኣዳዲስ ምርቶች ወደ ገቤ ለማስገባት በሚፈልጉበት ሰዓት ጉቦ በመክፈል በህግ ላይ የተመሰረቱ እንቅፋቶችን ለማለፍ ጥረት ያድረጋሉ። በሌላ መልኩም ድርጅቶች የሌሎች ፈጠራዎች ተቀባይነት እንዳያገኙና ወደ ገበያ እንዳይገቡ ለማድረግ ለተቆጣጣሪ አካላት ጎቦ በመክፈል ተወዳዳሪዎች ላይ ተፅኖ ሊያሳደሩ እንደሚችሉም ይገመታል። ከዚህ በመነሳት በፈጠራ ገበያ የሚታየው ሙስና በገበያው ያለው ውድደር ደረጃ ላይ የተመሰረተ ሊሆንም ይችላል (Fatma & Kevin, 2022)። ኣንዳነድ አጥኚዎች ሙስና ግትር የኢንቨስትመንት መሰናክሎች በማሰወገድና ፈጣርን በማበረታታት በምጣኔ ሃብት እድገት ላይ አወንታዊ ሚና ሊኖረው እንደሚችል አመላክተዋል። በተቃራኒው ደግሞ በሙስናና ፈጠራ መካከል ያለውን ግኑኝነት በምጣኔ ሃብት እድገት ላይ አሉታዊ ሚና ሊኖረው እንደሚችል አስገንዝበዋል (Roberto & Maria, 2022)።

ሌላው ከፈጠራ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የሚስና ጉዳይ ቦኖር የፈጠራ ባለቤትነት ህጋዊ ከለላ ለማግኘት የሚደረግ ጥረትን ያጠቃልላል። የንግድ ድርጅቶች የፈጠራ ባለቤትነት ምዝገባ በሚደርጉበት ጊዜ ጉዳያቸው እንዲፈጥንላቸው ለተቆጣጣሪ መንግስታዊ አካለት ክፍያ የመፈፀም ስራ እንደሚሰሩ ጥናቶች ያለመላከታሉ። በተጨማሪም የማማረቻ ድርጅቶች አከባቢቸውን የሚበክሉ ቴክኖሎጂዎች እንዳይጠቀሙ የሚደነገግወን ህግ ለመተላለፍ የሚያደርጉት ጥረት ጥቅማቸውን ለማካበት ወደ ሙስና ሊገቡ ይችላሉ(Global Development Institute, 2021)። በቻይና በ2015 የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ወደ 35% የሚሆኑት የንግድ ድርጀቶች ለመንግስት

ባለስልጣናት ጉቦ እንደሚከፍሉ አመላክተዋል፡፡ በተለይ በሪልስቴት እና አምራች ድርጅቶች ችግሩ ጎልቶ እንደሚታይ በዳሰሳው ተጠቅሷል፡፡ ይህም በገበያ ውስጥ ያለው ተወዳዳሪነት የመፍጠር አቅም ላይ ያልተመሰረተ ሊያደርገው ስለሚችል የንግድ ድርጅቶች ለምርምርና ጥናት የሚመድቡት በጀት አነስተኛ ሊያደርገው ይችላል ተብሎ ይታመናል(Thurnherr, 2020)፡፡ በተጨማሪም የአሜሪካው Congressional Research Service በ2020 ያቀረበው ሪፖርት እንደሚያሳየው በቻይና የንግድ ድርጅቶች የሚካየደውን የአእምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ጥሰቶች ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ያትታል፡፡ የሚፈፀሙት የአእምሯዊ ንብረት ጥሰቶችና ዝርፊያዎች ለመከላከል እንዲቻልም ተገቢው ህጋዊ መወሰድ እንዳለበት ሪፖረቱ አስገንዝቧል፡፡

ክፍል ሶስት

የጥናቱ መረጃ አሰባስብ ሂደትና ትንተና ዘዴ

3.1. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)

ሙስናና ብልሹ አሠራር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚያደርሰውን የሙስና ሥጋት ጥናት ለማካሄድ በአብዛኛው ዓይነታዊ እና በተወሰነ ደረጃ የአሃዛዊ (mixed approach) የጥናት ዘዴዎችን በማጣመር በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆነው መረጃም ከየካቲት 8 እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም የመሰብብ ስራ ተሰርቷል፡፡

3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)

ይህ ጥናት በዋነኝነት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ በሚገኙ አምስት (5) ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣ የህግ አገልግሎት፣ የለውጥና መልካም አስተዳደር፣ የአይሲቲ የጥናት መረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዘዴ ከወሳኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች መካከል የሆነውን ዓላማ ተኮር ዘዴን በመከተል የጥናቱ ተሳታፊዎችን የለየ ሲሆን በተቋማት ውስጥ ባሉ አሠራሮችና የስራ ሂደቶች ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሄደ ጥናት ነው፡፡

3.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)

3.3.1. የዝግጅት ምዕራፍ

በዚህ በዘርፍ ሥር በተደራጁት ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 11 የትኩረት ርእሰ ጉዳዮችን የመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የመረጃ መሰብሰቢ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በመጠይቅ ዙርያ ላይ ለመረጃ ሰበሳቢዎች ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎችም ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎች ለመሰብሰብ እንዲቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ በመፍጠር መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለጥናቱ ግብኣት የሚሆነው መረጃ የተሰበሰበባቸው የትኩረት ርዕሰ ጉዳዮችም ዝርዝር በሚቀጥለው ንኡስ ርእስ ቀርቧል፡፡

3.3.2. የሙስና ሥጋት መንስኤዎችንና አመላካቾችን ልየታ

የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ሲዘጋጅ ታሳቢ የተደረገው በተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት ሊያሳዩ የሚችሉ አመላካች ርዕሰ ጉዳዮች መለየት ነው፡፡ በዚህ እሳቤ መነሻነትም አስራ አንድ ተለየይተው የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቁ ተዘጋጅቷል፡፡ በዘርፉ በተደራጁት ተቋማት የትኩረት ርዕሰ ጉዳዩ ባለመከናወኑ ወይም ሲከናወን የተስተዋሉ ችግሮችን ከሙስና እና ብልሹ አሠራር አንፃር በመቃኘት የሙስና የስጋት መንስኤዎች ወይም አመላካች መረጃዎች መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያው መጠይቅ ውስጥ የተካተቱ ትኩረት የተሰጣቸው ርዕሰ ጎዳዮች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ተቋማዊ አደረጃጀት፡-** ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አስራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ተጠያቂነት፡-** ተቋማት ተልዕኳቸውን የህግ የበላይነትን በማረጋገጥና ተጠያቂነትን ለማስፈን የህግ ጥሰቶችን በህግ ስርዓት በማስተካከል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ግልፅነት፡-** የመንግስት ተቋማት የተቋቋሙበት ዋና አላማ ለህዝብ አገልግሎት መስጠት እስከሆነ ድረስ ተግባር፣ሃላፊነታቸውና የአሰራር ስርዓታቸውን ለተገልግጋዩ ማህበረሰብ ግልፅና ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት አገልሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተደራሽነት መርሆች ምን እደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ፡-** ሙስና እና ብልሹ አሰረሰርን ለመከላከል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣አፈፃፀምንን ለማሻሻል ተቋማት የአሰራር መመሪያ፣ አዋጅና ደንብ ያወጣሉእንዲሁም በየ ጊዜው ያሻሽላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት ቁመና ምን እንደምሚስልና የሚያወጧቸው የአሰራር መመሪያዎች ምን ያክል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ስለመናቸው የምንፈትሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ንብረት አስተዳደር፡-** የዘርፉ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡም ሆነ አገልግሎት የማይሰጡ፣ መወገድና መጠበቅ ያለባቸው የተቋማት ንብረቶች የተያዙበት ስርዓት ምን እንደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

- **ተቋማዊ የግዥ አስተዳደር፡** ግዥ በእቅድ፣በመመሪያና በቴክኖሎጅ በታገዘ መልኩ በመፈፀም ብልሹ አሰራርን የሚከላከሉበትን ስረዓትና አሰራር የመፈተሸበት የጥኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሰው ሃብት አስተዳደር፡** አቅምና ብቃት ያለው የሰውሃበት መረጃ አያያዝን እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ የሚያስተዳድሩብትን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሀብት ምዝገባ፡ ሀብት** ምዝገባ አንዱ የግልፅነትና ተጠያቂነት ማረጋገጫ መርህ ስለሆነ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሀብታቸውን ስለማስመዝገባቸው የምንፈሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ፕሮጀክት አስተዳደር፡** ተቋማት የሚያስተዳድሯቸውን ፕሮጀክቶች የሚያስተዳድሩበትና የሚቆጣጠሩበት ስርዓት ብክነትን በቀነሰ እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ስለመሆኑ የምንገመገምበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የኦዲት ቁጥጥር፡** የውስጥና የውጭ የኦዲት ግኝቶችን የሚገመገሙበት፣ ውይይት የሚደረግበት እንዲሁም የማስተካያ አስራሩ ምን እንደሚመስል ተቋማት የሚገመገምበት የትኩረት መስክ ነው
- **የተቋማትን ልዩ ተልዕኮ መሰረት ያደረገ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ልየታ፡** ተቋማት የጋራ ከሚያደርጓቸው የድጋፍ የስራ ክፍሎች በተጨማሪ የተቋቋሙት ልዩ ተልዕኮ ያላቸውን የተጋላጭነት ሁኔታ የተለየ የሚያደርገው በመሆኑ ልዩ የሆኑት የሚታዩበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

3.4. የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ

የተሰበሰበው መረጃ ከመተንተቱ በፊት ከየተቋማቱ መረጃዎች በርእሰ ጉዳች ከተለዩ በኂላ የማደራጃት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከተደራጀው የሰነድ መረጃ ለማውጣት (extract) እንዲቻል በየዘርፉ የጥናት ቡድኖች ተዘጋጅተው ስራው እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ መረጃው በማውታት ሂደትም በተለዩት ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ ተቋማቱ ማከናወን ሲገባቸው ያለከናወኑት ተግባር፣ ተግባራቱን ሲያከናወኑ የተስተዋሉ ችግሮችንና ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም በተግባራት ክንውን ወቅት የተስተዋሉ ለሙሰና የተጋለጡና ብልሹ አሰራሮች ለመለየት አስችሏል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለመተንተን እንዲቻል ከአሉት ዓይነታዊ መረጃ

አተናተኖች ውስጥ ጭብጥ ተኮር (Thematic Analysis) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ሪፖርት አቀራረብም አይነታዊ ገለፃ ዘዴ (Descriptive Method) ተግባራዊ የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በትንተናው ሂደትም መረጃዎች በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ተግዳረቶች ግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡ ይህም ድምዳሜ ላይ ከመድረሳችን በፊት ጥንቃቄ እንድናደርግ ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

ክፍል አራት

የሙስና ሥጋት መረጃዎች ትንተና

የኢኖቬሽን ቴክኖሎጅ ዘርፍ የሙስና ስጋት ትንተና በአስራ አንድ ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1 የተቋማት አደረጃጀት

በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ስር የሚገኙ አምስት ተቋማት ሁሉም የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸውን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የአቋቋሙ ሲሆን፣ በአማካይ 69 በመቶ የሚሆኑት የስራ መደቦች በሰው ሃይል የተሟሉ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአምስቱም ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ እቅድ በማዘጋጀትና ዕቅዳቸውን መሰረት በማድረግ እንደሚሰሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሁሉም ተቋማት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች የተሟሉ ሲሆን በጀትን በሚመለከት ደግሞ ፕሮፖዛል አዘጋጅተው ሲያቀርቡ የሚፈቀድበት አሰራር (ፑል ሲስተም) እየተተገበረ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሆኖም ከላይ ከተገለፁት ዝርዝር ሀሳቦች መከከል የሰው ሀይል አለመሟላት እና ቁርጥ በጀት አለመመደቡ በዘርፉ ስር የታዩ የአደረጃጀት ውስንነቶች ናቸው፡፡

በዘርፉ ተቋማት ከሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል በተጨማሪ የሀብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዥ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ… ወዘተ የተቋቋሙባቸው ደብዳቤዎች ተያይዟል፡፡ሆኖም ግን በተወሰኑ ተቋማት ውስጥ ብልሹ አሰራሮች ሲከሰቱ አጣርቶ ተጠርጣሪዎችን ለህግ የሚያቀርብ እና ተዛማጅ ስራዎችን የሚሰራ ራሱን የቻለ የህግ ባለሙያ የለም፡፡ በቴክኖሎጅ ዘርፍ ስር የሚገኙት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ከሌሎች የስራ ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት… ወዘተ) ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የተዘረጋ ሥርዓት ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡ ጥቆማ የተከሰቱ የሙስና ድርጊቶች እና ብልሹ ተግባራትን ለመለየት፣ ለማጣራት እና ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ

አይነተኛ የትግል መሳሪያ ነው፡፡ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል የሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ኢሜይል፣ ድረ-ገጽ እና ስልክ የመሳሰሉት ዘመናዊ የጥቆማ መስጫ መንገዶች እየተተገበሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሕግ ክፍል ራሱን ችሎ በተቋቋመባቸው ተቋማት ውስጥ (የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ጂኦ-ስፓሻል ኢንስቲትዩት፣ የኢኖቬሽን ቴክኖሎጅ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን) ውጫዊ እና ውስጣዊ ውሎች ላይ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ እንደሚደረግና ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት የአሠራር ሥርዓት እንዳለ ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በባዮና ኢመርጅንግ ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩ የህግ ባለሙያ ቢኖርም ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሰራር መረጃ አልቀረበም፡፡ እንዲሁም በአትዮጵያ ቴክኖሎጅ ባለስልጣን የህግ ባለሙያ ባለመኖሩ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት የአሠራር ስርዓት ስለመኖሩ የቀረበ አመላካች መረጃ የለም፡፡
በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት መኖሩን የሚያሳይ መረጃ ባይኖርም በአንድ ተቋም የህግ ባለሙያ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት ሥርዓት ባለመዘርጋቱ በጣልቃ-ገብነት ምክንያት ከስራው እንዲገለል መደረጉን አመላካች እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተሰጣቸውን ተልዕኮና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል በተለይ በሰው ሃይልና በጀት ቁመና ላይ የማይገኙ በመሆናቸው ለሥነ-ምግባር ጥሰቶችና እና የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ የስነምግባር ክፍል በሚፈለገው ደረጃ የሰው ሃይል አለሞሟላት የሚያመላክተው ዋናው ጉዳይ ሙስናንና ብልሹ አሰራር ለመዋጋት የሚደረገው ጥረት ላይ እክል ሊፈጥር መቻሉ ነው፡፡ በተጨማሪም የዘርፉ ተቋማት ለጉዳዩ የሰጡት ትኩረት አነስተኛ ያስመስለዋል፡፡ የበጅት ችግሩም የስነ ምግባር ክፍሉ በነፃነት ስራው በአግባቡ እንዳይሰራ ሊያደርገው መቻሉ ሳያንስ ለአመራሩ ጣልቃ ግብነት ሊጋልጠው ይችላል፡፡ ክፍሉ በጀት መጠቀም የሚችለው አመራሩ ሲፈቅድ ብቻ በመሆኑ

ስራዎች በአመራሩ በጎፍቃድ ላይ የተመሰረቱ ሊሆሁ የሚችሉበት እድል ሰፊ ይሆናል፡፡ ውጤቱም የመንግስት ስራ በአግባቡ ያለመምራት ችግር ለመኖሩ አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡

- ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል አጋዥ ከሆኑት የስራ ዘርፎች መካከል የህግ አገልገሎት ክፍል አስተዋፅኦና ሚና ከፍተኛ ቢሆንም በዘርፉ በሚገኙ የተወሰኑ ተቋማት የህግ ክፍሉን በሚፈለገው ደረጃ አሳታፊ አለማድረጋቸው ታይቷል፡፡ ስለሆነም በሚፈለገው ደረጃ በሰው ሃይል የተደራጀ ክፍል አለመኖር ተገቢው ህግነክ ምክር ለተለያዩ የስራ ክፍሎች መስጠት ስለማይቻል ተቋማቱን ለህግ ጥሰት ሊያድረጋቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ በዘርፉ ስር ባለ አንድ ተቋም የህግ ባለሙያ እያለ የህግና የውሎች አስተያየት የሚሰትበት ልም አለመኖር ውሎች ለህግ ጥሰት ሊጋለጡ እንደሚችሉ ማሳያ ነው፡፡ ስራውን የህግ ክፍል መኖር ተጠያቂነት ለማስፍን ካለው አስተዋፅኦ በተጨማሪ የቅድመ መከላከል ስራ ለመስራት የሚኖረው ሚና የጎላ ነው፡፡
- ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከ መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ እንዲሁም የጋራ ትንተና ለማካሄድ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን አመላካች ነው፡፡ ይህም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ሙስናን ለመዋጋት የሚደረገው ጥረት ውጤታማንት ላይ አሉታዊ ሚና ሊኖረው ይችላል፡፡ ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማደረግ ካልጠቻለም ሰራተኞች ለመሳተፍ የሚስችላቸውን መድረክ ስለሚጡ ሙስናን ለመዋጋት የሚደርጉት ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

4.2 ተቋማዊ ተጠያቂነት

በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የሙስና ስጋት ጥናት በሚመለከት የአሰራር ሥርዓት ጥናት በ3 ተቋማት እንደተካሄደ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ጥናት ከተካሄደባቸው ርዕሶች መካከል በግዥ፣ ሰው ሃብት፣ ዶክመንቴሽንና ፋይናንስ በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ ጥናት በተካሄደባቸው ጉዳዮች ላይ የተወሰኑ ማሻሻያዎች እንደተደረጉ ቢገለጽም ጥናቶች ያሳዩትን ውጤት/ማሻሻያዎች ሊያሣይ የሚችል ማስረጃ አልተያያዘም፡፡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ወይም ተቋማት ይህንን ከፍተኛ ፋይዳ ያለውን ተግባር (ጥናት) እንዲያከናውኑ በተጠያቂነት፣ በኃላፊነትና በአግባቡ እንዲወጡ የሚጠበቁ ተግባራት ትኩረት በማድረግ በጥናት በሚገኙ ግኝቶች ላይ ተሰርቶ

የማሻሻያ ጉዳዮች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው በመረጃ ሊደገፍ ይገባል፡፡ ሆኖም የደንበኞች እርካታ ላይ ጥናት አለመካሄዱ ከተጋልጋዮች በኩል የሚጋጥሙ ብልሹ አሰራሮች እና ከሙሰና ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ለመለየት ስራ አለመሰራቱ ያሳየል፡፡

በዘርፉ በሚገኙ አብዛኛዎቹ ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct) በህትመት ውጤቶች የተዘጋጁ ማስረጃዎች ቢገኙም የተዘጋጁበት ጊዜ የቆየ መሆኑ፤ በደንቡ የሰፈሩትን መሰረታዊ እሴቶች በሰራተኞች ውስጥ የማስረፅ፣ ስልጠናና ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎች ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ ከወቅታዊነታቸው አንጻር ጊዜ ያለፈባቸው በመሆኑ በአዲስ መልክ ሊሻሻሉ እና ለሰራተኞቻቸው ግንዛቤ የመፍጠር እንዲሁም የማጠናከር ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡ እንዲሁም መመሪያውን ለሰራተኞች ባግባቡ ተደራሽ ለማድረግ በስፋት እንዳልተከናወነ የተገኙ መረጃዎች ያሣያሉ፡፡ የአዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ተቋም ደንቡ ስለመዘጋጀቱ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ለሚገኙ ተቋማት ስለደንቡ ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ በበቂ ዝግጅትና በዕቅድ የተለዩ የግንዛቤ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ቀድሞ በመከላከል ረገድ የመረጃ ጥቆማዎች ከፍተኛ ፋይዳ እንደላቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ረገድ በዘርፉ በሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የቀረቡ (ዝርዝር ብዛት) ቅሬታዎች እና በህግ ክፍል የደረሱ የዲሲፕሊን ክስ ጉዳዮች እና ውሳኔ የተሰጣቸው የተወሰኑ ጥቆማዎችና ቅሬታዎች መኖራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህም ሁኔታ የቀረቡ ጥቆማዎች እና ክሶች በአግባቡ ውሳኔ ያላገኙ እንዳሉ ከቀረቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስለሆነም በሰራኞች ሥነ-ምግበር ደንብ፣ በስራ ሥነ-ምግባር፣ በጥቆማ አቀራረብና ፋይዳ እና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስራዎች በሰፊው ሊሰራ እንደሚገባ የሚጠቁም ነው፡፡ በተጨማሪም የበላይ ሃላፊዎች የስነምግባር ክፍሉ ስራዎች እና ተግባራት በመገምገም ተጠያቂነት ለማስፈን የሚያደርጉት እንቅስቃሴ መኖሩን የሚያሳይ በሰነድ የተደገፈ መረጃ አልተገኘም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- ተቋማት በአሰራራቸው ላይ የሙስና ስጋትን ለመቀነስ ከሚጠበቅባቸው ተልዕኮ አንዱ ጥናቶችን ማካሄድ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ውስን ጥናቶች የተካሔዱበት ሁኔታ ቢኖርም የችግሩ ስፋትና ጥልቀት በሚመጥን መልኩ አለመካሄዳቸው ጥናቶቹ ውስንነት ያለባቸው መሆኑን ማሳያ ነው፡፡ ጥልቅ ጥናት አለማከሄዱ ከልምድ ውስንነት ሊመነጭ የሚችል ቢሆንም ችግሮችን በጥናት ላይ ተመስርቶ መፍትሄ የመፈለግና የመስጠት ተቋማዊ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት አነስተኛ መሆን አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡ የተገልጋዮች ችግር በተጠና መንገድ ለይቶ እርምጃ መውሰድ ባህል አለመዳበሩም ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ውስንነት ያለው መሆኑ ያሳያል፡፡ ተገልጋዮች ተኮር ጥናት አለመካሄድም ተቋማት ማህበራዊ ተጠያቂነት ለማስፈን የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተቋማት ጥናት የማካሄድ ልምድ አለማዳበራቸው ኃላፊነታቸው በመወጣት ረገድ ሰፊ ክፍተት እንዳለ አመላካች ነው፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት ኃላፊዎች በአሰራር ሥርዓት ጥናት የሚቀርቡ የማሻሻያ ሀሳቦችን ተግባራዊ እንዲሆኑ በባለቤትነት ትኩረት ሰጥተው ክትትል ስለማያደርጉ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮች እንዲበራከቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- አብዛኛው ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ ያዘጋጁ መሆኑን በመልካም የሚወሰድ ልምድ ቢሆንም ከተግበራዊነቱ አንፃር ሲታይ አመርቂ ደረጃ ነው ብለን መውሰድ አንችልም፡፡ የአዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ተቋም ደንቡ ስለመዘጋጀቱ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ በትኩረት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ይሁንእንጂ የተዘጋጁት ሰነዶች ከወቅታዊነት አኳያ ውስንነት እንደሚስተዋልባቸው እና በአስፈፃሚው በኩል ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን መመልከት ተችሏል፡፡ በመሆኑ ደንቡ በአዲስ መልክ ሊሻሻል እና ለሰራተኞቻቸው ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ከተቋመት ይጠበቃል፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ተገባራዊ ተደርጎ ተጠያቂ የሆኑ ክፍሎች ወይም ሰራተኞች ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ድንቡ ተጠያቂነት ለማስፈን አለመቻሉ አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ተቋማት

የስነምግባሩ ደንቦች የማሻሻል ወይም አዲስ የማዘጋጀት ስራ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

- ቅሬታዎችና ጥቆማዎች የሚቀርቡበት ስርአት መዘርጋትና ተግባራዊነቱ መከታተል ብልሹ አሰራሮች ለመዋጋት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ ሙስናን አሳታፊ በሆነ መልኩ ለመዋጋት ድርሻው የጎላ ነው፡፡ ሰራተኞችና ተጋልጋዮች ክፍራቻ በፀዳ መልኩ ስለ ሙስናና ብልሹ አሰራር ቅሬታዎችና ጥቆማዎች ማቅረብ የሚችሉበት አሰራር የማረጋገጥ ስራ ከአመራሩ ይጠበቃል፡፡ የቅሬታና ጥቆማ ስራአቱ ውጤታማ አለመሆኑን መረዳት የሚቻለው የቀረቡ ጥቆማዎች እና ክሶች አጣርቶ እልባት የመስጠት በተቋማቱ ውስጥ የዳበረ አለመሆኑን ከተገኘው መረጃ መመልከት ይቻላል፡፡ ይኽም በመሆኑ ጥቆማዎችንና ክሶችን በወቅቱና በተገቢው መንገድ እልባት አለመስጠት ለመልካም አስተዳደርና ለሙስና በር ከመክፈቱ ባሻገር ጥቆማ የማቅረብ ፍላጎትና ተነሳሽነት ሊቀንሰው እንደሚችልም መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ የጥቆማ ስርአቱ ጠንካራ መሆን ካልቻለ በሌለ ስልጣን የመነገድና ጎዳዮች አላግባብ ከማጓተት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ሙስናዎችና ብልሹ አሰራሮች ለመዋጋት ያለው እድል ሊያመክነው ይችላል፡፡

4.3 የተቋማት ግልጽነት

የዘርፍ ግልፅነት ማለት የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ግልፅነትን የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የዘርፉን ተዓማኒነት እና ተቀባይነት ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡ የዘርፉን ግልፅነት ለማስፈን እንዲያግዝ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ እና ምልከታ መረዳት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት የተደረገበት መሆኑን ቃለ ጉባኤ የተያያዘ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ተቋማት የሩብ ዓመት የስድስት ወር፣ የ9 ወር ወይም ዓመታዊ ሪፖርቶች እንዳሏቸው እና የእቅድ አፈጻጸም ግምገማዎቹ ብልሹ አሰራሮችን ለመለየት ማስቻሉን በሪፖርቶች መመልከት ተችሏል፡፡ ተቋማቱ ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ

ለሚመለከታቻው አካላት ተደራሽ በማድረግ በኩል እየሰሩ መሆናቸውን ከተገኙት የስራ አፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ማየት ተችሏል፡፡

በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት ከማሳተፍ፣ ውሳኔዎች እና ቃለ-ጉባዔዎችን ደግሞ በተገቢው መንገድ ተደራሽ ከማድረግ አኳያ አብዛኞቹ የሚያሳትፉ ስለመሆናቸው እና ተደራሽ ስለማድረጋቸው የሚያሳይ የሰነድ መረጃዎች አልተገኙም፡፡ በዘርፉ ያሉ የተወሰኑ ተቋማት የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በይፋ የሚያሰራጩ ሲሆኑ ሌሎች በዘርፉ ያሉ ተቋማት ግን በይፋ ስለማሰራጨታቸው የሚያሳዩ ሰነዶችን ማግኘት አልተቻለም፡፡ ሁሉም ተቋማት የተቋማቸውን መረጃዎች የሚያሰራጩባቸው ማህበራዊ ወይም ድህረ-ገፅ እንዳላቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይሁንእንጂ ተቋማት ለምርመራ ጋዜጠኝነት ክፍት መሆናቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ከላይ ከቀረበው ተቋማዊ ተጠያቂነት ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- እቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች በየሩብ አመቱ የመገምገም ስራ እየተሰራ መሆኑን በበጎ የሚወሰድ ቢሆን ችግሮች ለይቶ እርምጃ በመውሰድ በኩል ያለው ቁርጠኝነት የሚያሳይ መረጃ ግን አልቀረበም፡፡ ይህም የሚወሰዱ ማስተካከያዎችና እርማቶች ግልፅነት የጎደላች ሊሆኑ እንደሚችሉ አመላካች ነው፡፡ ሌላው በተቋማቱ የሚስተዋለው ክፍተት የውሳኔ ቃለ ጉባኤዎች ተደራሽ አለመሆናቸው ግልፅነትን ከማሰፈን አንፃር ውስንነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የውሳኔ ቃለጉባኤዎች ተደራሽ አለመሆናቸው አመራሩ በስልጣን አላግባብ በመገልገል ውሳኔ ሲያሳልፍ ወይም ውሳኔዎች ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችልበት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ሙስናን ለመዋጋት ያለው እድል አዳጋች ያደርገዋል፡፡
- ተቋማት የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም ስለሚሰሯቸው ስራዎች ተደራሽ የሚያደርጉ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በተለይ በማህበራዊ ወይም ድህረ-ገፅ መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የማድረግ እየተሰራ መሆኑን ነው፡፡ ይሁንእንጂ መረጃዎች ተካታታይ በሆነ መንገድ ለባለድርሻ አካለት የማድረስ ውስንነት መኖሩን ከድህረ-ገፅ ምልከታ መረዳት ይቻልል፡፡ በድህረ-ገፅ ሚወጡ መረጃዎች ጊዜ ያለፈባቸውና በየጊዜው ማይታደሱ (not updated) መሆናቸው መመልከት ግልፅነት ለማስፈን

የሚደረገው ስራ አመርቂ አለመሆኑ ያሳያል፡፡ የአንዳንዶቹ ተቋማት ድህረ-ገፅም በተግባር እየሰሩ አለመሆናቸው የኢንተርኔት ዳሰሳ ማድረግ በቂ ነው፡፡ መረጃ ግልፅ በሆነ መንገድ ለባለድርሻ አካላትና ዜጎች ተደራሽ አለመሆኑ ሙስና እና ብልሹ አሰራር በመከላከል ረገድ ያላቸው አስተዋፅኦ ውስን እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

4.4 አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

በዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመታገል ከሚያስችሉ መሳሪያዎች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ የህግ የበላይነትን ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታቸውን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በጥናቶች እና ዕለት-ከዕለት ከሚሰሩ ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች በመነሳት አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ ከተወሰኑ ተቋማት ውጪ እየተሰራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም አብዛኛው ተቋማት በሚባል ደረጃ የስነ-ምግባር ደንቦችና ሙስና መከላከል የሚያስችሉ መመሪያዎች በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆናቸውን ከቀረቡ ሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚወጡ መመሪያዎችን በፍትህ ሚኒስቴር የማስመዝገብ ልምድ እየዳበረ መሆኑን ከተገኙት መረጃዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ፀድቀው በሚወጡ መመሪያዎችና ደንቦች ለተገልጋዮች/ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ ረገድ በማህበራዊ ሚዲያዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን ከተቋማቱ በተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን በዘርፉ ስር ካሉት ተቋማት መካከል ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና እየሰጡ ስለመሆኑ የሚያመላክት መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ሌላው አብዛኛዎቹ ተቋማት የዜጎች ቻርተርን በማዘጋጀት ለተገልጋዮች ተደራሽ ያደረጉ ሲሆን የተወሰኑት ግን ለተገልጋዮች ተደራሽ ስለማድረጋቸው መረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ ከተወሰኑ ተቋማት ውጪ እየተሰራ ባለመሆኑ የቁጥጥር ሥርዓቱን ስለሚቀንስ ለሙስና ስጋት ሊያጋልጥ የሚችልበት እድል ሰፊ ነው፡፡ የሙስና ከሁኔታዎች ጋር ያለው የተለዋዋጭነት ባህርይ ግምት ውስጥ ያስጋባ ህጎችን የማሻሻል ስራ መስራት ካልተቻል ውጤታማ መሆን አይቻልም፡፡ በተጨማሪም ተግባራዊ መደረጋቸው ብቻ በቂ ስለማይሆን ሙስናን ከመከላከል አንፃር ያመጡት ለውጥ ወይም የሚያሳድሩት ተፅኖ መመርመር እና ማጥናት ካልተቻለ ተጠያቂነት ለማስፈን ያላቸውን ጠቃሚነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይከተዋል፡፡
- ለሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል እና ሌሎች አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን እነዚህን ህጎች ለተቋማት ማህበረሰቡና ለተገልጋዮች የግንዛቤ ስራ በሚገባ ባለመሰራቱ እነዚህ አካላት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ሊኖራቸው የሚገባ ተሳትፎ እና ሚና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መረዳት ተችሏል፡፡ በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ይዘትና አተገባበር ዙርያ ለአመራሮች እና ሰራተኞች ስልጠና የመስጠት ባህል አለመዳበሩ በአፈፃፀም ላይ ክፍተት ከመፍጠሩ ባሻገር ህጎች አለአግባብ ሲጣሱ ለማረም የሚኖረው እድል ሊያጠበው ይችላል፡፡፡
- የዜጎች ቻርተር ያዘጋጁ ቢኖሩም ለተጠቃሚ ተዳረሽ በማድረግ በኩል የተሰራው ስራ ግን አጥጋቢ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ስለሆነም ዜጎች አገልግሎት በሚገኙበት ጊዜ ግዴታቸውና መብታቸውን ስለማያውቁ ለአላስፈላጊ እንግልትና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

4.5 የንብረት አስተዳደር ትንተና

የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ወጤታማነት የሚለካው ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ የተገዙ ንብረቶችን መረከብ፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅ፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ

መስራት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ያሉ ተቋማት የንብረት አስተዳደር ሥርዓትን በተመለከተ የቀረቡ ሰነዶች የንብረት ቆጠራ ስራ እየተሰራ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከንብረት አያያዝ ጋር የሚጠቀሰው ጉዳይ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ሲሆን ሥርዓቱ በዘርፉ ተቋማት ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ንብረት አያያዝን በተመለከተ ዘመናዊ አሰራር አለመኖር በንብረት አያያዝና ቁጥጥር ሥርዓት ላይ ክፍተት በመፍጠር የሙስና ስጋት ሊሆን ይችላል፡፡ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ እንደተቻለው አብዛኛው በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶችን የመለየት ስራ እንደሚሰሩ ተረጋግጧል፡፡ የሚወገዱ ንብረቶች ከመወገዳቸው በፊት አስቀድሞ በተዘጋጀ ስቶር ተገቢ ጥበቃ እና አያያዝ የሚደረግላቸው መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ንብረቶቹም በሽያጭ፣ በስጦታ/በድጋፍ እና በማቃጠል ወይም በመቅበር መልክ በሚመለከተው አካል ፀድቆ የማስወገድ ስራ ተሰርቷል፡፡ ነገር ግን የባዮ ኢመርጅንግ ቴክኖሎጂ ተቋም ንብረት ክፍል መወገድ የሚገባው ንብረቶች ተገቢ ጥበቃና አያያዝ እንዳልተደረገለት ለመመልከት ተችሏል፡፡ ይሁንእንጂ የንብረት አስተዳደር አውቶሜሽን ስራ የሚያመላክት መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- *በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት መወገድ የሚገባው ንብረቶች ተገቢ ጥበቃና አያያዝ ደካማ መሆን ሙስና እና ብልሹ ተግባራት ለመከላከል የሚያስችል ባለመሆኑ የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ ስርዓት ለሙስና ስጋት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ የንብረት አስተዳደር አሰራሩ በተገቢው ጥበቃና ቁጥጥር ካልታገዘ የመንግስት ንብረቶችን ለስርቆትና ብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ያደርገዋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የዘርፉ ተቋማት ተከታታይነት ባለው መንገድ የተሟላ ንብረት ቆጠራ እያካሄዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡*
- *የካይዘን ንብረት አስተዳተደር ስርኣት አለመተግበሩ የሃብት አሰተዳደሩ የመንግስት ንብረት ለብክነት የተጋለጠ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ካይዘን ዋና ዓላመው የሀብት*

ብክነትን መከላከል ነው፡፡ ንብረትን በተደራጀና አሳታፊ በሆነ መልኩ ለማስተዳደርና መቆጣጠር አስቻይ ሁኔታ በመፍጠር ሁሉም የተቋም የስራ ክፍሎች እና ሰራተኞች ሃብትን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል ያግዛል፡፡ ካይዘን አለመተግበሩ እቃዎች በክምችት እያሉና ስራ ላይ ሳይውሉ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን አላስፈላጊ ክምችትን በመፍጠር የህዝብ ሀብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በየተቋማቱ የንብረት አስተዳደር ስርኣቱ በአውቶሜሽን የታገዘ አለመሆኑን ለመግንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የንብረት አስተዳደር ዘመናዊ አሰራር የተከተለ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ይህም ስርቆትና ብክነት ለመከላከል የሚያስችለውን እድል ያመክነዋል፡፡

4.6 የግዥ አስተዳደር ትንተና

በዘርፉ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት በዘርፉ ስር ባሉ አብዛኛው መስሪያ ቤቶች የግዥ ሥርዓትና የግዥ አፈፃፀምን በተመለከተ የተሟላ መረጃ የሚሰጥ ኃላፊ ማግኘት በተለያዩ ምክንያቶች አስቸጋሪ ነበር፡፡ በዘርፉ ስር ባሉ ሁሉም ተቋማት የግዥ እቅድ እና የግዥ አፈፃፀም ላይ ግምገማ በማካሄድ የግምገማ ሰነድ መኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት ግዥ የሚከናወነው በእቅድ፤ ከየክፍሉ ያለን ፍላጎት መሰረት በማድረግ እንዲሁም ስቶክ ላይ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ስለመሆኑ በተደረገ ውይይት ግንዛቤ ቢኖርም በአብዛኛው ተቋማት ላይ ሒደቱን የሚያሳይ መረጃ ግን አልተገኘም፡፡ ተቋማቱ ከየክፍሉ የሰበሰቡትን ፍላጎትና በተቋም ደረጃ የሰሩትን ማጠቃለያ የሚያሳይ መረጃ ቢያደራጁ ለመረጃ ፈላጊ አካልና ለሚመለከታቸው አካላት ግልፀኝነትን ከማስፈኑ በተጨማሪ የግዥ ስርዓቱ ህግንና በዘፈቀደ የሚገዙ ግዥዎች ሊያመጡ የሚችሉትን የሙስና ስጋት ይቀንሳል፡፡

በዘርፉ ከግዥ በፊት የገበያ ጥናት ከማድረግ አኳያ ስንመለከት አብዛኛው በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት በተጠናከረ መልኩ እንደማያደርጉ እንዲሁም የገበያ ጥናት አድራጊ ኮሚቴም ማደራጀታቸውን የሚያሳይ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተወሰኑ ተቋማት የገበያ ጥናት እንደሚያደርጉ ቢገልፁም የገበያ ጥናት ማድረጋቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ግዥ የሚከናወነው በግዥ ኤጀንሲ ማዕቀፍ ስለሆነና

የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጠው ኤጀንሲው በመሆኑ የገበያ ጥናት ትርጉም የሌለው መሆኑን የተወሰኑ ተቋማት ገልፀዋል፡፡

በዘርፉ ባሉ ተቋማት የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ መሰረት ያለ ዕቅድ የሚገዙ ግዥዎች ቁጥራቸው ከፍተኛ ሲሆን፣ የቀጥታ ግዥዎች እና ከአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ እንደሚሰጥ በተደረገው ምልከታ ለማየት ተችሏል፡፡ በቀጥታ ግዥ ለመፈፀም መጀመሪያ መሟላት የሚጠበቅባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ የቀጥታ ግዥዎች እንዲካሄዱ የሚያሥገድድ ገፊ ምክንያት ሊኖር የሚችል ቢሆንም ግዥዎቹ ለምን በግልፅ ጨረታ እንዳልተከናወኑ፣ ሳይታቀዱ እንደተገዙና፣ ለምን ከአንድ አቅራቢ እንደተገዙ ምክንያቱን የሚገልፅ መረጃ አልተያያዘም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 በቀጥታ ግዥ መቼ እንደሚፈጸምና ከአንድ አቅራቢ መቼ ሊገዛ እንደሚችል በዝርዝር ያስቀመጠ ቢሆንም በዘርፉ የተገዙ የቀጥታና የአንድ አቅራቢ ግዥዎች ምክንያታዊ እንዲሆኑ አሳማኝ ምክንያቶች ሊቀመጥላቸው ይገባል፡፡

የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ e-GP በተመረጡ ድርጅቶች እንዲተገበሩ በያዘው አቅጣጫ መሰረት በዘርፉ ስር ባሉ መስሪያ ቤቶች የአተገባበር ስራዉ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የኤሌክትሮኒክ ግዥ መፈፀሚያ ሲስተሙ ተዘጋጅቶ የተላከላቸው ተቋማት በ2016 በጀት ዓመት ለመጀመር ያቀዱ እና የግዥ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ፀድቆ ወደ ሥራ እንዲገቡ የተደረጉ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ ተቋማት የe-GP ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሄዱበት ርቀት የሚያበረታታ ነው፡፡ ይህ የግዥ ስርዓት ሀብትን በቁጠባ ለመጠቀምና የግዥ ሥርዓቱን በእቅድ ከመምራት አንፃር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ሲሆን ያላጠናቀቁ ተቋማት የማዘመኑን ስራ በማጠናቀቅ ከማንዋል ሥራ ወደ ዲጂታል ሲስተም በፍጥነት እንዲቡ ግፊት ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- ለሙስና ተጋላጭ ከሆኑ የመንግስት ተግባራት አንዱ የመንግስት ግዥ መሆኑ እሙን ነው፡፡ የዚህ ምክንያቱ የግብይቶች ብዛት እና በውስጥ የሚታዩ የገንዘብ ፍላጎቶች እንዲሁም ከሂደቱ ውስብስብነት ጋር ተዳምሮ ሊሆን መቻሉ ነው፡፡ በተጨማሪም

በመንግስት ባለስልጣናት እና የንግድ ድርጅቶች መካካል የሚፈጠር መስተጋብራዊ ግኑኝነትም ሙስና እንዲከሰት ሊያደርግ ይችላል። ግዥዎች ከየሥራ ክፍሉ ያለን ፍላጎት መሰረት በማድረግ እንዲሁም ስቶክ ላይ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ አለመሆን አላስፈላጊ ግዥዎች እንዲፈፀሙ ሊያደርግ እንደሚችል ይታመናል። በተጨማሪም አብዛኛው በተቋማት የሚፈፀሙ ግዥዎች በገበያ ጥናት ላይ ያልተመሰረቱ መሆናቸው በምልክታ ለመገንብ ተችሏል። በተለይ ግዢዎች በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረቱ ካልሆኑ በተጋነነ ዋጋ ላይ ተመስርተው እንዲፈፀሙ ሊደረጉ መቻላቸው የሚጠበቅ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ግዥ በጥናት ላይ አለመመስረቱ የመንግስት ባለስልጣናት በጥቅም ግጭት ምክንያት ለሚፈጠሩዋቸው ሙሰናዎችና ብልሹ አሰራሮች ተገጋለጭ ሊያደርጋቸው ይችላል። ውጤቱም የመንግሰት ባለስጣናት የማይገባቸው ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ወደ እምነት ማጉደል ተግባራት ሊገቡ ይችላሉ። ያለ ዕቅድ የሚገዙ ግዥዎች ቁጥራቸው ከፍተኛ መሆኑ ሲታይ ሂደቱ ለህብት ብክነት የሚኖረው አስተዋፅኦ ክፍተኛ ሊሆን ይችላል። ከአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ ግዥዎች የሚፈፀሙበት ሁኔታዎች መኖራቸው ከፍተኛ የመንግስት መዋዕለ ንዋይ የሚፈስበት የስራ ዘርፍ ህጋዊ አሰራርና ስርዓትን ተከትሎ የማይሰራ ከሆነ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል። እንዲሁም ለጥቅም ግጭት ሊያጋልጥ ይችላል።

- ኤሌክትሮኒክ ግዥ ፈጣንና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ በመፍጠር የግዥ ሂደቶችን ቀላል እና ለአቅራቢዎች ወይም ለንግድ ማህበረሰብ እኩል እድሎችን በመስጠት የመንግስት ግዢን ግልፅነት የተላበሰ በማድረግ ብልሹ አሰራሮችን ለመቀነስ አስተዋፅኦው የጎላ ነው። የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ከተሰበሰበው መረጃ መገንዘብ ተችሏል። ይህ የግዢ አሰራር አቅራቢዎች እንዲመዘገቡ በማድረግ በየጊዜው መረጃ እንዲደርሳቸው በማደረግ በቂ ቁጥር ያለቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ አስቻይ ሁኔታ ከመፍጠሩ ባሻገር ሃላፊነታቸውን የማይወጡ አቅራቢዎች ላይ መረጃ በማመንጨት ሙሰናን ለመዋጋት አጋዥ ሚና ይጫወታል። የሰው ለሰው ንክኪ ስለሚቀንሰውም የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ከማድረግ በተጨማሪ የግዥ ሂደቱ ግልፅነት የተላበሰ እንዲሆን ስለሚያደርገው ሊከሰት የሚችለውን ሙስና በማስቀረት ድርሻው ከፍተኛ ነው።

4.7 የሰው ሀብት አስተዳደር

የዘርፉን ተቋማት ስኬት ከሚወስኑ መሰረታዊ ግብዓቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያላቸው የሰው ሀብት ነው፡፡ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ሀብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ውስጥ ያሉት ተቋማት የቅጥር፣ የዝውውር፣ የዲሲፒሊን ኮሚቴ በማቋቋም ስራ እየሰሩ መሆኑን ከተቋማት የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ስር ባሉት ተቋማት 38 ቅሬታዎች ቀርበው 28ቱ ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ቀሪ 10 ቅሬታዎች ውሳኔ ያላገኙ ናቸው፡፡ አፈፃፀሙም 74 በመቶ ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ በዘርፉ ቅሬታዎችን በማስተናገድ እና መፍትሔ በመስጠት በኩል አጥጋቢ ሊባል የሚችል ስራ መሰራቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም የቅጥር ማስታወቂያዎች በጋዜጣ፣ የተወሰኑ ተቋማት በድህረ-ገጽ፤ እንዲሁም ሁሉም ተቋማት የውስጥ ሰሌዳ ላይ እንዲለጠፍ በማድረግ ተደራሽ መደረጉን በተደረገው ምልከታ/የሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የሰራተኞች ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ስርዓትን በተከተለ መልኩ እየተሰራ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በዘርፉ የሚገኙ የሰራተኛ የሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ማጣራትን በተመለከተ የማጣራት ስራ ስለመሰራቱ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ የአመራር ሹመትና የሰራተኞች ምደባ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የተወሰኑ ተቋማት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተቀናጀ የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ሥርዓት (Integrated Civil Service Management Information system (ICSMIS)) በማበልፀግ ስራ ላይ ይገኛሉ፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት አብዛኛዎቹ ተቋማት የአቅም ግንባታ እና የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ስልጠና

የሚሰጥ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም በስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ላይ ተመስርተው ስለመካሄዳቸው ማሳያ የለም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- *ሀሰተኛ የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስረጃ ማረጋገጥ ስራ ሙሰናን ለመዋጋት ካለው ሚና አንፃር ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው፡፡ የማጣራቱና ማረጋገጥ ስራ በውስን መልኩ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ በዘርፉ ካለው የሰራተኛ ብዛት አኳያ የማጣራት ስራ አፈፃፀም አጥጋቢ አለመሆኑን ያመላክታል፡፡ ሃሰተኛ ሰነዶች በመጠቀም የሚቀጠሩ ሰራተኞች በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ከሚያስከትሉት ጉዳት ባሻገር ጉዳዩ የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነድ በማስመሰል የማዘጋጀት ሙስና መፈፀሙ አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሀሰተኛ የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስረጃዎች የዜጎች የስራ እድል በመዝጋት ልምድና እውቀት ዋጋ እንዲያጣ ስለሚያደርገው በመንግስታዊ ቅጥር በብቃት ያልተመሰረተ እንዲሆን ሊያደርግ መቻሉ ሰፊ ነው፡፡ ውጤቱም ዜጎች በመንግስት አገልግሎት ላይ ያላቸው እምነት ሊሸረሽረው ይችላል፡፡*
- *ዘርፉ ለአገር ካለዉ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ከሚያንቀሳቅሰዉ ሀብትና ተጋላጭነት አኳያ የሰዉ ሃብት ብቃት እና ስነምግባር ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን በፍላጎት ዳሰሳ ላይ ተመስርቶ የመስጠት ክፍተት እንዳለ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ከእውቀት ማነስ የሚፈጠሩ ብልሹ አሰራሮች እና ድካማ አፈፃፀሞች በር መክፈቱ የሚጠበቅ ነው፡፡ በተለይ በስነምግባር ዙርያ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን የዘርፉ አመራር መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡ ለስልጠና የሚያስፈልግም ሀብት መመደብም ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በሰራተኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በሚፈለገው ደረጃ ምላሽ አለመስጠት የሚስተዋል መሆኑ የስራ ተነሳሽነትና እርካታ ላይ አሉታዊ ውጤት ሊኖረው ከመቻሉ ባሻገር ሙስና በመከላከል በኩል የሚያደርጉት ተሳትፎ ሊቀንሰው ይችላል፡፡ በተቋማት የሰው ሃብት አስተዳዳሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ በማደረግ በኩል ያለው እንቅስቃሴም አጥጋቢ አለመሆኑን መታዘብ ይቻላል፡፡*

4.8 የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

ዘመናዊ ከሆኑ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከያ ስልቶች መካከል አንዱ የሚመለከታቸው አካላት የሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥርዓት ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ዓይነተኛ መሳሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህም መሰረት በሃገራችን ላለፉት 10 ዓመታት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣን ሃብታቸውና ንብረታቸውን ማሳወቅና ማስመዝገብ እንዳለባቸው የህግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

በመሆኑም በዘርፉ ከተካተቱ ተቋማት መካከል የ4 ተቋማት ሰራተኞችና ባለስልጣናት ሃብታቸውን የማሳወቅና የማስመዝገብ ስራዎች ከ1258 መመዝገብ ከነበረባቸው ሰራተኛና ኃላፊዎች የተመዘገቡት 531 ብቻ (42%) መሆናቸውን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ባዮ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ግን ምንም አይነት የሀብት ምዝገባ ሥራ ስለመከናወኑ የቀረበ መረጃ የለም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ያለባቸው የተወሰኑ ሰራተኞችና የስራ ኃላፊዎች ቢኖሩም በውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች የተነሳ የተዘረጋው ሥርዓት ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑንና ለሙስና ስጋት ሊያጋልጥ የሚችልበት እድል ሊኖር እንደሚችል ያመላክታል፡፡ በዘመናዊ የታገዘ ውጤታማ ምዝገባ ማካሄድ ከተቻለ ምንጩ ያለታወቀ ንብረትና ገንዘብ ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆኑን በመገንዘብ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

4.9 የፕሮጀክት አስተዳደር

ባለፉት አምስት አመታት በዘርፉ ስር ባሉ አራት ተቋማት ውስጥ በፕሮጀክት የተሰሩ ስራዎች አለመኖሩን ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማዎቅ ተችሏል፡፡ ለኢት/ስፔስ ሳይንስና ጅኦ-ስፔሻል ቴክኖሎጅ አገልግሎት የሚውል የቡራዩ ሞዴል ኢኖቬሽን ቴክኖሎጅ ማዕከል ተጀምሮ በጊዜው ያላለቀ እና ተጨማሪ ስራ የተሰጠበት ፕሮጀክቶች ያለ ሲሆን በገንዘብ 472,852,098.01 ብር ነው፡፡ እንዲሁም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ ሚ/ር ከላይ ያለውን ፕሮጀክት የሚከታተል በመሆኑ

154,308,000.00 ብር የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት እንደሆነ ከቀረቡ መረጃዎች ለማዎቅ ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- በዘርፉ እየተተገበሩ ያሉት ፕሮጀክቶች በሚፈለገው መንገድ እየተጠናቀቁ አለመሆናቸውና ተጨማሪ ወጪ እየጠየቁ መሆናቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለፕሮጀክቶች የዋጋ ማሰተካካያ ተደርጎ የማስቀጠል ስራ እየተሰራ መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ያለው የፕሮጀክቶች አስተዳደር ስርኣቱ በአግባቡ ካልተማራም ለሙሰና ተጋላጭ ሊያደርጋቸው መቻሉ ይታመናል፡፡ መፀደቅ የማየይገባቸው ጨረታዎች በማፅደቅ ወይም ማሸነፍ የማይጋባቸው ተጫራጭች እንዲያሸንፉ በማደረግ የሚከሰት ብልሹ አሰራር ሊኖር ይችላል፡፡ ውጤቱም የመንግሰት ፕሮጀክቶች በተመደበላቸው በጀት እና ጊዜ እንዳይጠናቀቁ በማድረግ የህዝብ ሀብት ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡ ሆኖም የሚፈጠሩ ችግሮች ከሙስናና ብልሹ አሰራር የሚመነጩ ናቸው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ በመሆኑ በፕሮጀክት አስተዳደር ዙርያ የሚታዩ ችግሮች ለመፍታት ጥልቅ የሙስና ስጋት ጥናት ተገቢ ያደርገዋል፡፡ ይህም ችግሮቹ በመረጃና ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ያለውን እድል የያሰፋዋል፡፡

4.10 ኦዲትና ቁጥጥር

ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና ሕጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ የፋይናንስና ንብረት ክንውን የውስጥ ኦዲት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የስራቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ የውጭ ኦዲተር የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡ በዘርፉ ተቋማት የኦዲት አስተዳደር ሥርዓት በጥናቱ የታየ ሲሆን በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ዉስጥ ባሉ ድርጅቶች ያለው አሰራር እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡ በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት በየአመቱ የውስጥ ኦዲትና ቁጥጥር ስራ እየሰሩ መሆናቸዉን በተደረገው የሰነድ ማረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በየተቋማቱ ያሉ አመራሮች የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ የሚያደርጉ መሆኑን በተደረገው የሰነድ ማስረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ ለአብነት የሚከተሉት ከኦዲት ሪፖርት የተገኙ ግኝቶች መመልከት ይቻላል፡፡ -

- የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ያለ አግባብ የተወሰደ ብር 31,677.30 ሲኖር ከዚህ ውስጥ ብር 29,853.37 ተመላሽ መደረጉ፣
- የኢኖቬሽን ቴክኖሎጅ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ቴክኖሎጅ ባለስልጣን ያልተወራረደ ብር 417,628,766.15 በውስጥ ኦዲተር የተመላከተ መሆኑን ካቀረቡት ሰነዶች መረዳት ተችሏል፡፡

በዘርፉ ያሉ ተቋማት በኦዲት ግኝቶች ላይ ማሻሻያዎች የሚያደርጉ ሲሆን ለማስረጃነት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር የተደረገው የመረጃ ልውውጥ ደብዳቤ እና በተቋሙ የውስጥ አዲተሮች በየሩብ አመቱ የሚደረጉ ውይይቶች ላይ የታዩ ማሻሻያች በቃለ-ጉባኤ በአባሪነት ቀርቧል፡፡ የኦዲት ሪፖርት ተደራሽነትን በተመለከተ በዘርፉ ዉስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ተቋማት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተደራሽ የሚያደርጉ ሲሆን ለሌሎች የስራ ክፍሎች ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር ልምድ አለመኖሩን ከተጻፉ የኦዲት ሪፖርት ደብዳቤዎች ለማየት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር ያለ አንድ ተቋም ግን ለሚመለከታቸው ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ተደራሽ ማድረጉን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የሒሳብ አያያዝ ሥርዓትን ከማሻሻል አንፃር የፋይናንስ መረጃ አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ ወደ ተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት ለማስገባት የተደረጉ ሙከራዎች በተወሰኑ ተቋማት ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ አሰራር በትክክል እየተተገበረ መሆኑን በግልፅ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ግን ማግኘት አልተቻለም፡፡ የፋይናንስ አሠራር ሂደትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ ፈጣንና ቀልጣፋ አሠራር እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር የዘርፉ ተቋማት ለተግባራዊነቱ አስፈላጊ ጥረቶችን ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- የኦዲትና ቁጥጥር ስርዓት የመንግስትን ሀብት ከብክነት ለመታደግ፤ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመከላከል ያለው ሚና የጎላ ነው፡፡ አመራሩም በግኝቶች ላይ ተመስርቶ ክፍተቶች መሙላትና እና የቀረቡት ችግሮች ለመፍታት የእርምት ስራ መተግበር ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም ግኝት ላይ ተመስርተው የተወሰዱ እርምጃዎች የሚሳይ መረጃ በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይህም ብልሹ አሰራሮች ከማረም ባሻግር ተጠየያቂነት ለማስፈን የሚያስችል የሚያስችል ስራ እየተሰራ አለመሆን

የሚያመላክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች በቀላሉ ተደራሽ መሆናቸው የሚያሳይ መረጃም አልቀረበም፡፡ ሪፖርቶች ተደራሽ አለመሆናቸው አመራሩ አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት ያለው ተነሳሽነት ውስን መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም ተቋማት የውስጥና ውጭ ኦዲት ሪፖርቶች በቀላሉ ለባለድርሻ አካላት መድረስ የሚችልበት ሁኔታ በመፍጠር ሃላፊነታቸው መወጣት አለባቸው፡፡

- የኦዲት ሪፖርት በተመለከተም ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ አካላት በተለይም ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ ለህግ ፣ለተቋማዊ ለዉጥና የመገናኛ ብዙሃን በተደራጀ መልኩ ተደራሽ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ ይህም የሙስና ስጋቶች በጋራ በመየት የተቀናጀ ስልትና ፖሊሲ በመንደፍ በተቋም ደረጃ ሙስናን የመከላከል ስራ ለመከወን አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከመከላከል አንጻር ከላይ የተጠቀሱት ክፍሎች በቅንጅት እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ከዘርፉ ተቋማት አመራሮች የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

4.11 የሙስና ስጋት ትንተና

ተ.ቁ	የሙስና ስጋት የሆኑ ሂደቶች	የመከሰት ዕድል	ቢከሰት የሚያመጣው ተጽዕኖ	የስጋቱ መንስኤዎች	የመፍትሄ ሃሳቦች
1	ግዥ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	➢ ዋጋ አጋኖ ማቅረብ ➢ ለእቃ ጥራት ትኩረት አለመስጠት ➢ የስነ-ምግባር ችግር እና ሲስተም አለመኖር ➢ የጥራት የሀብት ብክነት ➢ የሐገሪቱ የግዥ ህጎች ➢ የተቆራረጠ ግዥ	➢ አብዛኛውን ግዥ በግልፅ ጨረታ መፈፀም ➢ ማንኛውም የግዥ ሥርዓት ህግና ደንብን ተከትሎ እንዲሆንና የዕቃ ጥራትና ዋጋ ላይ አለመደራደር መስፈን አለበት ➢ የስነ-ምግባር ችግርን ማስተካከል እና ሲስተም መዘርጋት ➢ በህጉ መሠረት የግዥ ሥርዓቱ መከናወን ይገባዋል ➢ የሀገሪቱን የግዥ ህግ መቀየር

2	ፋይናንስ	መካከለኛ	ከፍተኛ	➢ የጥራት ➢ የሀብት ብክነት ➢ ገንዘብ ያለበት በመሆኑ ➢ ክፍያ ሂደት ➢ ዋጋ አጋኖ ማቅረብ ➢ ለእቃ ጥራት ትኩረት	➢ የደመወዝና አበል ክፍያ፣ የተለያዩ ወጪዎች የተሟላ ሰነድ ቀርቦ ሊከፈል ይገባዋል ➢ ህግና አሰራር ➢ መመሪያዎችን ማሻሻልና ተግባራዊነታቸዉን መከታተል ➢ አብዛኛውን ግዥ በግልፅ ጨረታ መፈፀም ➢ ማንኛውም የግዥ ሥርዓት ህግና ደንብን ተከትሎ እንዲሆንና የዕቃ ጥራትና ዋጋ
3	የብቃትና ሰው ሀብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ	መካከለኛ	መካከለኛ	➢ ቅጥር፣ ምደባ፣ ደረጃ እድገት፣ ከመመሪያ ውጭ መፈፀም፣ ፎርጅድ የትምህርት	➢ በየግዜው የተሰሩ ቅጥር፣ ምደባ፣ ደረጃ እድገት ክትትል ማድረግ እና እርምት መስጠት ➢ ህጉን መሠረት ያደረረገ ቅጥር የደረጃ እድገት የተጠባባቂ አሰጣጥ መዋቅር በህጉ መሠረት መከናወን ይገባዋል
4	የመሰረታዊ ስራ አስፈጻሚ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	➢ የጥራት ➢ የሀብት ብክነት ➢ ንረት ያለበት በመሆኑ ➢ ንብረቶችን ማስተዳደር ለተፈለገዉ አላማ ማዋል	➢ የነዳጅ አጠቃቀም - ተሽከርካሪ አያያዝ ወቅታዊ ክትትል ሊደረግ ይገባዋል ➢ አሰራን ማጎልበት ➢ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ፣ያልተቆራረጠ ክትትልና አሰራሮችን ማዘመን ❖ ሁሉም የዘርፉ ተቋማት
5	ንግድ ምልክት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	➢ የሚሰጡ ማስረጃዎች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መሆናቸው	➢ ኃላፊንት በየደረጃው እንዲናረ ማድረግና ማስተማር ❖ አዕምሯዊ ንብረት
6	በደንበኞች አስተዳደር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	➢ ባለው የውጭ ደንበኞች አያያዝና ➢ የደንበኞች ቅሬታ	➢ ኃላፊንት በየደረጃው እንዲናረ ማድረግና ማስተማር ❖ አዕምሯዊ ንብረት
7	ትሪቡናል	መካከለኛ	ከፍተኛ	➢ ባለው የውጭ ደንበኞች አያያዝና ➢ የደንበኞች ቅሬታ	➢ ኃላፊንት በየደረጃው እንዲናረ ማድረግና ማስተማር ❖ አዕምሯዊ ንብረት

8	ከፍተኛ የፕሮጀክት ስራዎች	ከፍተኛ	ከፍተኛ	➢ በትውውቅና የተሰራ ፕሮጀክት እንደገና የተወሰነ ተጨምሮበት ቀርቦ ከፍተኛ	➢ ቅን መሆንና ለሀገር ማሰብ መቻል ➢ ግልጽ አሰራር ❖ ባዮ ኢመርጅንግና ኢኖቬሽን ቴ/ሚ/ር
9	አይሲተና ዲጂታል ኢኮኖሚ ዘርፍ	ከፍተኛ		➢ የአገልግሎት ና ጥራት	➢ አመቺ አሰራርን መፍጠር

ክፍል አምስት

መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ

5.1. መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የነበረው፣ በማዕድን ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመዳሰስ የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ በዚህ አቢይ ዓላማ ስር በጥናቱ መቋጫ ላይ ምላሽ ያገኛሉ ተብለው የታሰቡ አምስት የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህም፦ 1ኛ. የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣ 2ኛ. የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣ እና 3ኛ. ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በሪፖረቱ ላይ ከቀረቡትን አበይት የጥናቱ ውጤቶች መሰረት በማድረግየሚከተለው ድምዳሜ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

1. በዘርፉ አንድ የስነምገባር ክፍል ሶሥቱን ተቋማት እንዲከታተል መደረጉ ሳያንስ በበቂ የሰው ሃይል ያልተደራጀ መሆኑን መረዳት ግድ ይላል፡፡ ሙስና ብልሹ አሰራር ለመዋጋት የሚያስችል ቅንጅታዊ መደበኛ አሰራር አለመኖሩ እና ስነምግባር ክፍሉ በቀጥታ ተጠሪነቱ ለተቋም አመራር መሆኑን ለጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ስለሚያድረጋቸው ተግባራቸውና ሃላፊነታቸው ለመወጣት እክል ሊፈጥርባቸው እንደሚችል ነው፡፡
2. በጥናት ላይ የተመሰረተ ተቋማዊ ተጠያቂነት ስራ እየተሰራ አለመሆኑን በሙስና ስጋት ዙርያ እና በተገልጋዮች እርከታ ላይ ጥልቀት ያላቸው አለመካሄዳቸው እንደማሳያ ሊቅርቡ ይችላሉ፡፡ ሙስና እና ብልሹ አሰራር አሳታፊ በሆነ መልኩ የመዋጋት ልምድ አለመዳበሩም ይታያል፡፡
3. የመረጃ ተደራሽነት ሰራዎችም እስከ ሰራተኛው ድረስ ማረጋገጥ የሚያስችሉ ግልፅነትን ማሰፈን የሚያስችሉ ስራዎች መመልከት አልተቻለም፡፡ በአብዛኛው የእቅድና አፈፃፀም መረጃዎችና ሪፖረቶች በከፍተኛና መካከለኛ አመራሩ አከባቢ ላይ ተንጠልጥሎ የመቅረት ልምድ እንዳለ ለማስታዋል ተችሏል፡፡

4. በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ዙርያ ለአስፈፃሚው አካል ስለጠና የመስጠት ልምዱ አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ህጎችን ለማሻሻልና አዳዲስ ለማውጣት የሚያስችሉ አስፈላጊ ጥናቶች የማካሄድ ስራ ተግባራዊ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡
5. በተቋማቱ ያለው የንብረት አስተዳደር ለማዘመን የሚያስችሉ የካይዘን ስርኣት እና የአውተሜሽን ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተስተውሏል፡፡
6. አብዛኛው የተቋማት ግዝዎች በቁጥቁጥ መንገድ የሚፈፀሙ መሆናቸውን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ግዥዎች ያለ እቅድ የመፈፀም ሁኔታዎችም ታይቷል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ተስተውሏል፡፡
7. በዘርፉ ተቋማት ውስጥ ሀሰተኛ የትምህርትና ስራ ልምድ ሰነዶች የማጣራት ስራ ተተግብሯል ማለት አይቻልም፡፡ በተጨማሪም በፍላጎት ዳሰሳ ላይ የተመሰረተ የስነምግባር እና አቅም ግንባታ ስለጠና አየተሰጠ አመሆኑን መረጃዎች ያመላከታሉ፡፡
8. የፐሮጀክት አስተዳደር እና አተገባባር ላይ ውስንነት እንዳለ መመልከት ይቻላል፡፡ ተጨማሪ ክፍያዎች የመከፈል ሁኔታም ይታያል፡፡
9. ሃብት የማሳወቅና ማስመዝገብ ስራ አጥጋቢ ሊባል በሚል ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑን እና ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት መረዳት ተገቢ ነው፡፡
10. የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ አለመሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮች እና ሙሰናን ለመዋጋት የሚስችል ሁኔታ አለመፈጠሩ ነው፡፡

5.2. የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ

በዚህ ውስን ዳሰሳና ትንተና ጥልቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ቢያስቸግርም የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

- የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተሟላ የሰው ኃይል እንዲኖራቸው ማድረግ ቢቻል፣
- የህግ ባለሙያዎች ባልተመደበባቸው ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ስርዓት እንዲኖር ማድረግ ቢቻል፣

- የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን በበላይ ሃላፊዎች ሊገመገምና ግብረ-መልስ ሊሰጠው ይገባል፣ በተለያ የስራ ክፍሎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን መዘርጋትና ማጠናከር፣
- በቅሬታ አፈታት ላይ የሚታየው ውስንነት ለሰራተኛው እርካታ መቀነስ ብሎም ለደንበኞች አገልግሎት መዳከም ጉልህ አስተዋፅኦ ስለሚያደርግ የማሻሻያ ስርአት ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን ለመለየትና የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ ወቅቱን የጠበቀ የሙስና ስጋት ጥናት ማድረግ ይገባቸዋል፣ በተጨማሪም የደንበኞች እርካታ ጥናት በማካሄድ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑትን የስራ ሂደቶች በመለያት አስፈላጊውን ማሻሻያ ማድረግ፣
- ለሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል እና ሌሎች አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በተቋማት ለማህበረሰቡና ለተገልጋዮች የግንዛቤ ስራ በአግባቡ መስራት ቢቻል፣
- የወረቀት ሥራ ለተደጋጋሚ አካላዊ ግንኙነት እና ለሙስና ስጋት ሊጋብዝ የሚችል በመሆኑ ዲጂታላይዝድ ሲስተሞችን መዘርጋት (የአውቶሜሽን ስራዎችን ትኩረት ሰጥቶ ማበልፀግና መተግበር) ፣ ተገልጋዮችም በሲስተሞች እንዲጠቀሙ የግንዛቤ ስራ መስራት፣
- ከግልፅ ጨረታ ውጪ የሚካሄድ ግዥዎች (የቁጥ ቁጥ ግዢ፣ ከአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ መግዛት፣ የፕሮፎርማ ግዥ መብዛት ወዘተ) እንዲሁም ያለዕቅድ የሚከናወኑ ግዥዎች ለሙስና ስጋት የሚያጋልጡ ስለሚሆኑ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ የሚቻልበትን አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ቢቻል፡፡ ማንኛዉም ግዥ ከመከናወኑ በፊት የገበያ ጥናት የዋጋና የአይነት እውነታዎችን ስለሚያመላክት ቢለመድ፣
- ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ በማከናወን ተቋማት ያለበቂ ዕውቀትና ችሎታ ተቀጥረው ከሚያገለግሉ ሰራተኞች የመለየት ሥራ ቢሰራ፣
- በተቋማት መወገድ የሚገባው ንብረቶች ተገቢ ጥበቃና አያያዝ እና የካይዘን ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ ቢቻል፣
- የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓቶች የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል፣ ምንጫቸው ያልታወቀ ንብረቶችን ለመለየት እና ሰፊ የህዝብ አገልግሎት ታማኝነትን ለመገንባት

ሁለገብ መሳሪያ ናቸው፡፡ ስለዚህም የዘርፉ ተቋማት ይህን ስርአት በአፋጣኝ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ፕሮጀክቶች በአግባቡ መተግበራቸው አስፈላጊውን ክትትል በማደረግ አፈፃፀማቸውን የተሻለ እንዲሆን ማደረግ ተገቢ ነው፡፡ የሚታዩ ችግሮች ካሉም በጥናት ላይ ተመስርቶ የማረም ስራም ከተቋማት ይጠበቃል፡፡
- በኦዲት ግኝቶች ላይ ተመስርቶ አስፈላጊውን አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ በወቅቱ የመውሰድ እና የማስተካከል እና የማሻሻል ባህል ማዳበር ቢቻል፣

Reference

1. Golla, Julia (2010) *How strong is the influence of Corruption on Innovation, especially in post-communist EU Member States? - A Comparative Analysis.* https://essay.utwente.nl/60313/ accessed on April 20, 2023
2. Fatma Nur Karaman Kabadurmus & Kevin Sylwester, (2022) *Corruption and innovation: the importance of competition*, International Journal of Emerging Markets, Emerald Group Publishing Limited, vol. 17(3), pages 766-788.
3. Roberto Iorio & Maria Luigia Segnana, 2022. "Is paying bribes worthwhile? Corruption and innovation in middle-income countries," Eurasian Business Review, Springer; Eurasia Business and Economics Society, vol. 12(3), pages 475-504,
4. Global Development Institute (2021, November) Corruption And Innovation II: Green Innovations Around The World Http://Blog.Gdi.Manchester.Ac.Uk/Corruption-And-Innovation-Ii-Green-Innovations-Around-The-World/
5. Thurnherr, Sonia (2020) Corruption and Innovation Capability: a correlation analysis in 140 countries and its implications in international business, Global Risk Profile (https://globalriskprofile.com/wp-content/uploads/2020/10/CorruptionInnovation_LongVersion.pdf accessed on April 21, 2023)
6. Congressional Research Service (2020, September) Intellectual Property Violations and China: Legal Remedies, CRS Report Prepared For Members And Committees Of Congress (https://sgp.fas.org/crs/row/R46532.pdf accessed on April 21, 2023)